ሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-
Richard Montgomery High School

# የአለም አቀፍ ባከላኡሬት ማግኔት ፕሮግራም
# International Baccalaureate Magnet Programme

ለ9-12 ክፍሎች




250 Richard Montgomery Drive
Rockville, MD 20852
(301) 610-8100


ማመልከቻዎች በድረ-ገጽ www.montgomeryschoolsmd.org/curriculum/specialprograms ይገኛሉ

Montgomery County Public Schools

Rockville, Maryland

## የዓለም አቀፍ ባኮሎሪያ/International Baccalaureate ምንድን ነው?

ዓለም አቀፍ ባኮሎሪያ/International Baccalaureate® (IB) በተማሪ ላይ ያተኮረ አትራፊ ያልሆነ፣ ተልዕኮ ያለው፣ የትምህርት ፋውንዴሽን ነው። በ1968 ተመስርቶ፣ IB በአሁኑ ጊዜ እድሜያቸው ከ3 እስከ 19 አመት ለሆኑ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ተማሪዎች አራት ተፈታታኝ ፕሮግራሞችን ለማዘጋጀት እና ለማቅረብ በ153 ሀገራት ውስጥ ከሚገኙ 3,182 ት/ቤቶች ጋር ይሰራል። እነዚህ ፕሮግራሞች አእምሮአዊ፣ ግላዊ፣ ስሜታዊ እና ማህበራዊ ክሂሎቶችን ለሁሉም ተማሪዎች ያዳብራሉ፣ ተማሪዎችን በፍጥነት በመዋሃድ በሚገኝ አለም እንዲኖሩ፣ እንዲማሩ እና እንዲሰሩ ያዘጋጃሉ። ስለ IBና ፕሮግራሞቹ ተጨማሪ መረጃዎች፣ እባካችሁ በድርጅቱ ድርጣቢያ www.ibo.org ተጣቀሱ።

## IB በRichard Montgomery High School

ሪቻርድ ሞንትጎመሪ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት-Richard Montgomery High School (RMHS) የሚገኘው የIB ፕሮግራም ጠንካራ ቅድመ-ዩኒቨርስቲ የጥናቶች ኮርስ ለመከታተል ፍላጎት ላላቸው ባለከፍተኛ ችሎታና ቃል የገቡ ተማሪዎች የካውንቲ-አቀፍ ፕሮግራም ሆኖ በ1987 ተቋቋመ። ፕሮግራሙ ቀስ በቀስ በ Montgomery County ከሁሉም በላይ ወደ የተሟላ የIB ዲፕሎማ ፕሮግራምነት አደገ፣ እናም በአገር-አቀፍ ደረጃ እውቅና ያለው የ IB አካዴሚያዊ ተሞክሮ ሆኖ ይቀጥላል።

ፕሮግራሙን በስኬት የጨረሱ ተማሪዎች የ MCPS ዲፕሎማንና በአለም-አቀፍ ደረጃ እውቅና ያገኛ የ IB ዲፕሎማ ያገኛሉ። በርካታ ተማሪዎች በመረጧቸው የአለም ቋንቋዎች ችሎታቸውን/ብቃታቸውን በማሣየታቸው ምክንያት ከ IBO የሁለትዮሽ ቋንቋ ዲፕሎማ ያገኛሉ።

## የምርጫ ሂደቱ እንዴት ነው?

አጣሪ ኮሚቴው ሁሉንም ማመልከቻዎች በጥንቃቄ ገምግሞ ሚዛናቸው በተጠበቀ የፈተና ውጤቶች፣ የመምህር አስተያየቶች፣ ውጤቶች፣ እና የተቀስቃሽነት/የተነሳሽነት ማስረጃዎች በመመስረት ተማሪዎችን ይመርጣል።

## ማን ሊያመለክት ይችላል?

የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ሊያመለከቱ ይችላሉ፡-

- የሞንትጎመሪ ካውንቲ/Montgomery County ነዋሪነት።
- ቢያንስ በአልጀብራ 1 መመዝገብ።
- ቢያንስ የመጀመሪያ ደረጃ I ስፓንሽ/Spanish፣ ፈረንሳይኛ/French፣ ወይም ቻይኛኛ/Chinese ሁለት ቋንቋ ከእነዚህ ቋንቋዎች በአንዱ የገባ/የተመዘገበ

## የማግኔት እና የ IB ስርአተ ትምህርቶች ምንድን ናቸው?




የ IB መካከለኛ ዓመት ፕሮግራም ሞዴል ለ9ኛ እኛ 10ኛ ክፍል ተማሪዎች በ11ኛና 12ኛ ክፍሎች ለሚገኘው ለሁለት-ዓመት የ IB ዲፕሎማ ፕሮግራም ለማዘጋጀት ይሰጣል። የማግኔት ተማሪዎች እንግሊዘኛ፣ አንድ የአለም ቋንቋ፣ የህብረተሰብ ጥናቶችች፣ ሳይንስ፣ እና የሂሳብ ትምህርት፣ እንዲሁም ከሚሚያ ተመርጠው ከሚወሰዱት ውስጥ መርጠው እንዲወስዱ ይጠየቃሉ። የ IB ርእሶች እና የስርአተትምህርት መሰረቶች በማግኔት ፕሮግራም የመጀመርያዎቹ ሁለት ዓመቶች ስርአተትምህርት ጋር ተዋህደዋል/ተጣምረዋል።




IBO የ IB ዲፕሎማ ተማሪን እንደ አንድ የ11ኛ ወይም የ12ኛ ክፍል ተማሪ እንደሆነ/ች አድርጎ ይገልፃል። ስለሆነም፣ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የመጨረሻዎቹ ሁለት አመታት፣ ተማሪዎች በተለይም ለ IB ፈተናዎች እና ዲፕሎማ መስፈርቶች ይዘጋጃሉ። በመለስተኛ/junior እና ከፍተኛ/ senior አመታት የሚሰጡ ኮርሶች ጥያቄን፣ ይዘትን፣ የፅሁፍ ክሂሎትን፣ ወሳኝ አስተሳሰብን፣ እና በስድስቱ የትምህርት አይነት ቡድኖች የፅንስ ሀሳብ ትግበራ ላይ አጠናክረው ይቀጥላሉ። Theory of Knowledge course, Creativity, Activity, and Service/የእውቀት ንድፈ ሃሳብ ኮርስ፣ ፈጠራዊነት፣ እንቅስቃሴ፣ እና አገልግሎት (CAS) እና Extended Essay/የተራዘመ ድርሰት ፕሮግራሙን ያስጨርሱታል።

# ፈተናዎች

ተማሪዎች የ IB ፈተናዎችን በ Standard Level/መደበኛ ደረጃ (SL) በ11ኛ እና 12ኛ ክፍሎች እንደዚሁም Higher Level/በከፍተኛ ደረጃ (HL) በ12ኛ ክፍል ሊወስዱ ይችላሉ። እታች የሚገኘው ሰንጠረዥ በ RMHS ከሚሰጡት የ IB የትምህርት አይነቶችን የጥናት ደረጃን ያሳያል።

| ቡድን | መደበኛ ደረጃ | ከፍተኛ ደረጃ |
| --- | --- | --- |
| 1 | | እንግሊዘኛ |
| 2 | ቻይኒዝ<br>ፈረንሳይኛ<br>ስፓኒሽ | ቻይኒዝ<br>ፈረንሳይኛ<br>ስፓኒሽ<br>ባለ-ሁለት ቋንቋ |
| 3 | ታሪክ<br>የህብረተሰብ አንትሮፖሎጂ<br>ኤኮኖሚክስ<br>ስነ-ልቦና/ሳይኮሎጂ<br>ኣለም-አቀፍ ፖለቲካዎች | ታሪክ |
| 4 | ባዮሎጂ<br>ኬምስትሪ<br>ፊዝክስ<br>አካባቢያዊ/Environmental<br>ስርአቶች እና ህብረተሰቦች | ባዮሎጂ<br>ኬምስትሪ<br>ፊዝክስ |
| 5 | የሂሳብ ትምህርት<br>የሂሳብ ጥናቶች | የሂሳብ ትምህርት |
| 6 | ኪነት እና ንድፍ<br>የኮምፒዩተር ሳይንስ<br>ፊልም<br>ትያትር<br>A 2ኛ ቡድን 2፣ 3፣ ወይም 4 | ጥበብ እና ንድፍ<br>የኮምፒዩተር ሳይንስ<br>ፊልም<br>ትያትር<br>A 2ኛ ቡድን 2፣ 3፣ ወይም 4 |

# የ IB ዲፕሎማ መስፈርቶች ምንድን ናቸው?

ለ IB ዲፕሎማ ብቃት ለሚሟላት፣ ተማሪዎች በመለስተኛ እና ከፍተኛ (የትምህርት ደረጃ) ኣመቶቻቸው የሚከተሉትን መስፈርቶች በተሳካ ሁኔታ ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

- የኮርስ ስራ እና የ IB ፈተና መስፈርቶችን ማጠናቀቅ።
- ከ IB ርእስ መስኮች በአንዱ ረጅም ድርሰት መጻፍ።
- ወሳኝ የአስተሳሰብ ክህሎቶች ለማዳበር የተተለመውን፣ የእውቀት ፅንሰ ሃሳብ፣ የ IBን የተመሰከረለት ኮርስን ማጠናቀቅ።
- ከመማሪያ ክፍል ውጭ የልምድ ትምህርት ለማራመድ የተቀረጸውን የ CASን ተግባራትን ማጠናቀቅ።

# ተጨማሪ መረጃ

ስለ ኣለም-አቀፍ ባካሎርየት ማግኔት ተጨማሪ መረጃዎችን ለማግኘት፣ እባክዎ በስልክ ቁጥር፡- (301) 610-8100 ያግኙን።

Montgomery County Public Schools
Rockville, Maryland

በመገልገያ እቃዎች/ቁሳቁሶች አስተዳደር መምሪያ የኮንሶርሽያ ን/ክፍል የዝንባሌ ምርጫና ማመልከቻ ፕሮግራም አገልግሎት ታተመ።
Department of Materials Management for the
Division of Consortia Choice and Application Program Services (DCCAPS)

ትርጉም፡- Language Assistance Services Unit • Department of Communications

0019.19ct • Editorial ፣ Graphics & Publishing Services • 8/18 •2K